በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር እንዲያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና ። ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አልላከውምና። በእርሱ በሚያምን አይፈረድበትም ፡ በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል ። ዮሐንስ 3፡ 16-18

የህይወት እንጀራ እና መንገድ

ኢየሱስም እንዲህ አላቸው የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም በእኔ የሚያምንም ሁልጊዜ ከቶ አይጠማም ። ዮሐንስ 6፡32

እኔ መንገድና እውነት ህይወትም ነኝ ፡ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።
ዮሐንስ 14፡6

ኢየሱስ ከሌለ ሃማኖት እራሱ ገዳይ ነው ፡ ደም ግባት እና ዝና ከንቱ ነው። ያለማወቅ ሰውን ወደ ጨለማ ሲያመጣ ፣ ያሳዝናል ሰው ኢየሱስ ካላመነ መጨረሻ ጨለማ ነው ፣ ሰው እግዚአብሔር ካላወቀ ።

ፍቅር አንድነትን ሲያመጣ !
ደስታ ይመጣል በሀዘን ወስጥ ለሚኖር ሰው !
መራራ ይጣፍጣል ጥላቻ ሲጠፋ በሀገር !
እውነት ሲገለጥ ውሸት ሲወገድ ጨለማ ይጠፋል ብርሃን ሲመጣ !
ለቅሶ ሲበቃ ኢየሱስ ሲመጣ ሰላም ስገባ ይጣፍጣል መራራ !
ፍቅር እውነት ነው !
እውነት ደስታ ነው !
ደስታ ሰላም ነው !
ሰላም ኢየሱስ ነው !
ኢየሱስ አምላክ ነው !
አምላክ እግዚአብሔር ነው !
እግዚአብሔርም መንፈስ ቅዱስ ነው !

ቀስተደመና ነው በምድር ላይ የኛ ነው የምንለው ነገር ! አይ ሰው ዛሬ የኛ ነው የምንለው ነገር ነገ የሌላ ስይሆን ፤ የምንመካበት የኛ ነገር በአይን አይተን የማንጠግቦ ነገር ፤ ሰው በስንት መከራ አልፎ ወደ ክብር ሲመጣ ፤ በድካም ውጠት ባለንብረት አባት ሲሆን ፤ ሀብታምና ታወቅ ሰው ይሆናል ! አንድ ተማሪ በብዙ አመት ድካም በኃ ዶክተር እና እንጂነር ለመሆን ደረጃ ሲደረስ እና ባለስልጣን ስሆን ፤ እኔ ልዩ ሰው ነኝ ብሎ መመካት ይጀምራል ፣ ከከፍታ ሲወርድ የሰው ልጅ ዝና እና ሀብት ከንቱ ይሆናል ፥ የጊዜ ነገር ነው ሰውን በምድረ በዳ ላይ የሚያስቀር ነገር ፣ ከአንድ ደቂቃ በኃ ምን እንደሚፈጠር ሳያቅ የሰው ልጅ ፣ ዝና እና ሀብት አለ ብሎ መመካት ፣ አይ ያሳዝናል የሰው ልጅ ከላይ አሪንጓዴ ለብሶ ከጊዜ በኃ አፈር ሲለብስ ፣ ለጊዜ ነገር መመካት ባዶ ያስቀራል የሰው ልጅን ፥ ቀስተደመና ነው የያዘው ነገር ።

ለድንቅና ለታምራት ከሆነ እግዚአብሔር የምናምነው ፥ ፍቅር የሌለ ትዳር መልክና ሀብት አይቶ ከተጋቡ በኋ ፣ በመጨረሻ ባልና ሚስት ንብረት ለመካፈልና ለመለያየት ቢሮ ቀንና ለሊት እንደምሮጡ ነው የኛ ነገር ፤ ለድንቅና ለታምራት እግዚአብሔር ያመነ ሰው ፥ ችግር ቢበዛ መከራ መቋቋም አይችልም ፥ ሌላ ድንቅና ታምራት ያለ ቦታ መሄድ አይቀርም ፤ እንደዚህ አይነት ሰው ከእግዚአብሔር ህብረት ተቋርጦ ፥ ድንቅና ታምራት አምላክ የሚያደርግ ሰው ነው ፤ አንድ ሰው ሴት ልጅ ከልብ የምወድ ከሆነ ፥ በሽተኛ ብትሆንም ፥ ልራቅ አይችልም ምክንያቱ እሷን ከልብ ስለምወድ ፥ አንድ ላይ በፍቅር ይኖራልና ! የሰው ልጅ ክብር ሁሉ ትቶ ፣ የኢየሱስ ፍቅር ብቻ አይቶ ፣ እግዚአብሔር ካመነ ፣ የፈለገ መከራ ብመጣ ፣ ከእግዚአብሔር ህብረት አይርቅም ፣ መከራ ቢበዛ በትዕግሥት ሁሉንም ያሳልፋል ፣ ፍቅር ያወቀ ሰው እግዚአብሔር ያመነ ሰው ነው ማለት ነው ፤ ምክንያቱ እግዚአብሔር ፍቅር ስለሆነ ።

መራራ ነው የሰው ልጅ ህይወት ፣ ለመለወጥ ቀንና ለሊት ቢሮጥ !
መቸ ይሞላል የዚህ ምድር ነገር ፥ አንዱ አገኘሁት ስል አንዱን ማጣት ፤
እንቅልፍ ማጣት ወደ ስኬት ለመድረስ ፣ በሽታ ነው እንጅ መቸ እርካታ ይሆናል
፤ ሰው በእውቀት ትልቅ ቦታ ለመድረስ ፣ እንቅልፍ ማጣት አይደለም ወደ
ስኬት የሚያደርስ ፣ እግዚአብሔር ለኛ ያዘጋጀ ነገር ካልሆነ እኛ የምንሰራ ነገር
እና ወደ ስኬት ለመድረስ ቀንና ለሊት በድካም ጊዘ የምናሳልፈው ነገር ፤
ለመንከራተት ብቻ ነው እንጅ ወደ ስኬት ለመድረስ አይደለም የኛ እቅድ ፤
አምላክ ከሌለ ከኛ ጋራ ፣ የዓለም ብቸና ተወዳጅ ሰው ብንሆን ፣ ምን ጥቅም
አለ የኛ ህይወት ፣ ከመንግሥት ሰማይ ከጎደለ ፥ ሁሉ ከንቱ አይደለም ወይ
እግዚአብሔር ከኛ ጋር ከሌለ ፣ ባዶ ነው ህይወት ፣ ጨለማ ውስጥ ከኖረ ።

ፀሐይ ሲወጣ እንደሚያበራ ለሁሉ ቦታ ! እግዚአብሔር ያልሰጠ ነገር ምን አለ
ሀጢያት ነው እንጅ ሰውን በጨለማ ውስጥ ያስቀረ !
ዝናብ ሲዘንብ ለጎረቤት ዘንቦ መቸ አጠገብ ላለ ሰው ሳይዘብ ቀረ !
ቅናት ነው እንጂ ሰውን ወደኃላ ያስቀረ !
ወደላይ እግዚአብሔርን ሲመለከት ስገባ የሰው ልጅ ፣ አጠገብ ያለ ሰው
መቅናት ጀመረ ሳይለወጥ በከንቱ ዘመን ለመጨረስ !
መቸ የሰው ልጅ ተራ ሰው ሆኖ ይኖር ነበረ በዝ ምድር ላይ ፤
የእግዚአብሔር ቃል መሰማት እንቢ ስላለ ነው እንጂ የሰው ልጅ ፤
ራቆት አይቀርም ነበረ በዝ ምድር ላይ ።

የትዳር ትርጉም አይደለም ገንዘብና እውቀት ! እግዚአብሔር ጥሩ ትዳር ካልሰጠ ቁንጅና እና መልክ አያፀናም የፍቅር ጥልቀት !
መሳቅ ጥንድ ሆና ያምራል ሴትና ወንድ ፣ የሚያምር ፈገግታ አይዘልቅም ሁል ቀን ፣ መከራ ስመጣ ቀን ምሽት ይሆናል ፣ ነገር ሁሉ ግራ ይገባል ! ለሰው የማይቻል ለእግዚአብሔር ይቻላል ትዳር ውስጥ አምላክ መፈራት መከራ ያስረሳል ! መልክ እውቀትና ሀብት አይቶ ባለትዳር የምሆን ሰው ፤ ከጥቂት ጊዜ በኃ ወደ መከራ ውስጥ መገባት አይቀርም ፤ ምክንያቱ ከእግዚአብሔር ያልሆነ ነገር መጨረሻ ወደ መጥፎ አቅጣጫ ነው የሚወስደው ፣ ትዳር ያለ ፍቅር ፣ እሳት ውስጥ የወደቀ ቅቤ ማለት ነው ።

የሰው ትልቅነት ቁጣ በመቆጣጠር
ላይ እንጅ አይደለም በመጣለት !
ምላስ አይችለም ክፉ ከአፍ ሳያወጣ
ግን ጥበበኛ በዝምታ ያሸንፋል በከባድ ሁነታ !
ሰው አይን ስውር ነው ራይ ሳይኖር ሲቀር
በቤተሰብ ሸክም ከመሆን በቀር አይጠቅምም ለሀገር !
መሮጥ ሳይሆን መድረስ ነው የሚጠቅም ፤
ጉልበት ሳይሆን ጥብብ ነው ሰው የሚለውጥ !

ወንጌል እኛ ለወጠ !
ዛሬ ላይ አደረሰ !
መከራ ከኛ ላይ አስወገደ !
አሮጌ ታሪክ ከኛ ቀየረ !
በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት አደረገ !

ዛሬ ጠንክሮ ያልሰራ
ነገ ስኬታማ መሆን አይችልም !
የሚጣፍጥ ምግብ እያለ
መራራ ለመብላት ማን ይመኛል !
ወደፊት ለመራመድ ወደኋላ ማን ነው የሚመለስ !
በእጅ ያለ ነገር መልቀቅ ሳይሆን
በልብ ያለ ክፉ ነገር
ማስወገድ ነው ወደ ክብር የሚያደርስ !

በባዶ ቤት ሲሞላ ክብረ !
ለካ ህልም ነው እኔ ያየሁት ነገረ !
ስነቃ ህልሜ ለካ ባዶነት ነው የማይለወጥ ማንነቴ !
በእጅ ያለ ሲመስለን ክብረ !
ለካ ምኞት ነው የኔ ድካሜ !

ሩቅ ነው ሀገረ !
የዛሬ አይቼ እንዳይመልጥ የነገ !
የምድር ክብር እንደ ልብስ ለብሼ !
ከሰማይ ክብር እንዳልቀረ እኔ !
ሩቅ ሩቅ እያየሁት !
የቅርብ የሚመስለን ምኞቴ !

ያለ እግዚአብሔር የሆነ
የት አለ ዛሬ ላይ የታየ
ሰይጣን ነው የኔ ነገር አበላሸ
እንላለን ግን የኛ በደል
አወቀ ለጥፋት በምህረት ሳንቀርብ ወደ አምላክ !
በራሳችን በደል ተውጠን እንቀራለን
እኛ ሳንለወጥ !
ምኞት ሰውን ሳጠምድ !
ላያደረስ ወደ ክብር !
ሳያሳድድ ወደ ጥልቅ !
ወደኃላ አስቀረ ላይለውጥ !

የዓለም ነገር ሰውን አያረካም!
እንዴን አገኘሁ ስባል ለላ ማጣት!
ልብን ለማርካት ስኬታማ ለመሆን!
ቀንና ለሊት መሮጥ ለመለወጥ!
በድካም በተገኘ ውጠት!
እርካታ አገኘሁ ስል የሰው ልጅ!
የመከራ ጎርፍ ስገባ ወደ ቤት!
ለላ ነገር ለማገኘት ስመኝ!
በእጅ ያለ ነገር ሲነጠቅ!
እሳት ውስጥ እንደ ወደቀ ቅቤ!
ሰው የኔ ነው የምል ነገር ባዶ ስይሆን!
ላይሞላ ሲጎድል ድካም!
እርካታ የት አለ ከሌለ አምላክ!

የት አለ ክብር!
የሞላ ሲጎድል!
እያደከመ ላያደስት!
ተስፋ ስያስቆርጥ !
ላይሞላ ጎዶሎ ሆኖ!
ቀር የዚህ ምድር ነገር !
በህልውና በመገኘት ውጭ!
የት አለ ክብር ከሌለ አምላክ!
በአይን ከሚታይ በእጅ ከሚዳሰስ!
ከምድራዊ ሀብት አይገኝም ክብር!
የሰው ናፍቆት ላይረካ ሁለ ስመኝ!
ግብ ነው ምኞት!
ላያደርስ ወደ ስኬት !

መልካም ማድረግ ለራስ
ክፉ አታድርግ ለወዳጅ
ለጥቅም ብለ በጎ
ነገር ለማድረግ አትውደድ
የሰራ ያጭዳል የሰው ልጅ
ለጠላትም ብሆን መልካም
ከማድረግ ወደኃላ አትበል
በምድር በምታደርገው መልካም ነገር
በሰማይ ክብር ይጠብቃል አንተን !!!

ሙሉ ሆኖ አካል ከኖረ
ጎዶሎ የት አለ ሰላም ካለ
ሰላምን ሰጠ አምላክ
ክፋትን ለማስወገድ በፍቅር
የማይታመን በብር ሆኖ
ተገኘ የሰው ፍቅር
ከጥፍር እስከ ጸጉር
ሙሉ ከሆነ አካል
ምን አጎደለ አምላክ
መውጣትና መግባት
ያማረ ከሆነ መዋል
ከዚህ በላይ የት
አለ ክብር
አምላክ እኛ ከጠበቀ ከክፋት
ጠና ነው ሀብት
ፍቅር ነው ስኬት !

የሰው መንገድ ጠማማ
ላያዘልቅ ወደ ስኬት
በምኞት ሲያስቀር ድካም
የት አለ በረከት
ወደኋላ ሲያስቀር ከግብ
ባዶነት አይደለም ወይ
ከአምላክ መንገድ ውጭ መጓዝ !

እኔ የወይን ተክል ነኝ ፤ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ ። ማንም በእኔ ብኖር እኔም በእርሱ ብኖር ፣ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል ፣ ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና ። ዮሐንስ 15፡5

ሩጫ ብቻ ሆኖ
የሰው መንገድ ፊት
ለፊት ለማየት ስኬት
መታገል በራስ መንገድ
ላያ ደረስ ወደ ግብ
ወደ ፊት የምንሄደው መስሎ
ወደኋላ ሲያስቀር በውድቀት
ያማረ የመሰለ መንገድ
ከሠማይ ክብር እኛ ሲያስቀር
ከንቱ አይደለም ወይ
የዚህ ዓለም ጥበብ
እንመለስ ወደ መገኘት
ይሻለኛል በሞኝነት መኖር
እንምረጥ የአምላክ መንገድ
ለኛ ህይወት የምሆን
እርሱ የኛ መድሀኒት ኢየሱስ !!!

መላክ የሚመስል ፍጥረት
ድንቅ ነው
የሰው ልጅ ውበት
የማያልፍ እየመሰለ ሲያጎመጅ
ሰውን ሳጠምድ እንደ ወጥመድ
ላያ ዘልቅ የሰው ደም ግባት
ስወለድ የሰው ልጅ
ድንቅ ነው ውበት
ያማረ ካል ሆነ ፍጻሜ
ውድቀት ነው ከፊት ያለ
ባዶ ነው ህይወት
ያለ አምላክ የት አለና
ለሰው ልጅ ክብር !

ስሜትን ለመረዳት ራስን
ለሃጢኣት ወጥመድ መዘርጋት
ከለላ ያደርጋል ከክብር
ወደኋላ ያስቀራል ከለውጥ
አን ጋዝ እንደ ምኞት
ያርቃል እኛ ከህይወት መንገድ
መራራ ቢሆን ሁሉ ነገር
ፍጻሜ ተስፋ አለ
ከአምላክ ዘንድ ክብር

- አገልግሎትን መደገፍ የምትፈልገው ካላቸው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
- የአካውንት ቁጥር 1000187312087 የስልክ ቁጥር 0928756030 ዘላለም ብርሃኑ